# Mod-HSA

**ልጅዎን እና አስተማሪውን/ዋን ለግምገማ ለመዘጋጀት ምን አድርገው መርዳት ይችላሉ?**

የልጅዎን አስተማሪ በአስፈለገ ቁጥር ስለልጅዎ ትምህርት ሂደት ለማነጋገር ያግኙት። ልጅዎ እና እርስዎ ቤት ውስጥ ልትሠሯቸው የምትችሏ ቸው፣ ለግምገማዎቹ የሚያዘጋጁና ልጅዎን በቤት ሥራ በይበልጥ የሚረዱ እንቅስቃሴዎች አስተማሪዎ እንዲጠቁም ይጠይቁት። IEP ውስጥ በተገለጸው መሠረት ተማሪው በክፍል ውስጥ እና በግምገማዎች ላይ ተገቢው መቀመጫ እንደተዘጋጀለት አስተማሪዎችና ወላጆች/አሳዳጊዎች ማረጋገጥ አለባቸው። ወላጆች/አሳዳጊዎች እና አስተማሪዎች ተባብረው ሲሠሩ ተማሪዎች ይጠቀማሉ። በይበልጥ መረጃ ለማግኘት እና የ Mod-HSA ፈተና ምሳሌዎች ለማግኘት www.mdk12.orgን ይጎብኙ።

**ለMod-HSA ውጤቶች ሪፖርት የሚደረጉት እንዴት ነው?**

የMod-HSA ውጤት ሪፖርት እና የቤት ሪፖርቶች አከፋፈል ከመደበኛው HSA ሪፖርት ጋር በተመሳሳይ የጊዜ ሰሌዳ ላይ ይደረጋሉ። የትምህርት ቤቶች፣ የአካባቢ ትምህርት ሥርዓቶች እና የስቴቱ ውጤት መረጃ በኢንተርኔት አድራሻ www.mdreportcard.org በሚገኘው ዓመታዊው "የትምህርት ሪፖርት ካርድ" ላይ ይታተማል። በይበልጥ መረጃ ለማግኘት እባክዎን የልጅዎን ትምህርት ቤት ይገናኙ።



Nancy S. Grasmick
የስቴት ትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ

James H. DeGraffenreidt, Jr.
የሜሪላንድ ስቴት ትምህርት ቦርድ ሊቀመንበር

Martin O'Malley
የሜሪላንድ ስቴት አገረ ገዢ

ይህ ሰነድ በሜሪላንድ ስቴት ማሻሻያ የገንዘብ ስጦታ ሥር፣ በልዩ ትምህርት ክፍል/አስቀድሞ ችግር መፍቻ አገልግሎቶች፣ ችሮታ ቁጥር H373X070019 አማካኝነት ዳብሮና ታትሞ የተዘጋጀ ነው። እዚህ ውስጥ የተገለጹት አመለካከቶች በግድ የዩ.ኤስ. የትምህርት መምሪያ ወይም የማንኛውም ሌላ የፌዴራል ድርጅትን የሚያንጸባርቁ ስላልሆኑ እንደዛ መታየት የለባቸውም። የልዩ ትምህርት ክፍል/አስቀድሞ ችግር መፍቻ አገልግሎቶች ከዩ.ኤስ. ትምህርት መምሪያ፣ ልዩ ትምህርትና ማገገሚያ አገልግሎቶች ቢሮ የገንዘብ ድጋፍ ያገኛል። ይህ መረጃ ከሕትመት ሕግ (ኮፒራይት) ነጻ ነው። አንባቢዎች አባዝተው መጋራት ይችላሉ ሆኖም እባካችሁ ከሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ፣ የልዩ ትምህርት ክፍል/አስቀድሞ ችግር መፍቻ አገልግሎቶች የመጣ መሆኑን አስታውቁ።

Maryland State Department of Education
200 West Baltimore Street
Division of Special Education/Early Intervention Services
Baltimore, Maryland 21201- 2595

(410) 767-0249 (ስልክ)
(410) 333-6442 (መስማት ለሚሳናቸው)
(410) 333-8165 (ፋክስ)
*© Maryland State Department of Education 2008*


*01/09*

# የተሻሻለው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግምገማ (Mod-HSA)

## ለልጅዎ ፕሮግራም ያለው ትርጉም ምን እንደሆነ



# MOD-HSA



# የተሻሻለው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግምገማ ወይም Mod-HSA የወላጅ መምሪያ

## Mod-HSAዎች ምንድን ናቸው?

Mod-HSAዎች በየትምህርት ደረጃ ዋና የትምህርት ዓላማዎች የይዞታ መስፈርትና በተሻሻለ የትምህርት ውጤት መስፈርቶች ላይ የተመሠረቱ አማራጭ ግምገማዎች ሲሆኑ የታቀዱትም የተወሰኑ የተሳትፎ መስፈርቶችን ለሚያሟሉ፣ የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ለሚያገኙ ተማሪዎች ነው። እነዚህ በትምህርት ማለቂያ የሚሰጡ የአልጄብራ/መረጃ መተንተን፣ የእንግሊዝኛ፣ የባዮሎጂ እና የአስተዳደር ግምገማዎች የሜሪላንድ መመረቂይ ፈተና መስፈርቶችን ያሟላሉ (*መጀመሪያ 9ኛ ክፍል የገቡት በ2005 ዓ.ም. በልግ ላይ ወይም ከዛ በኋላ ለሆኑ ተማሪዎች HSAዎችን ማለፍ ግዴታ ነው*)።

የMod-HSAዎች ይዞታ (በሜሪላንድ ዋና ትምህርት ዓላማዎች እና የግምገማ ገደብ ውስጥ በተገለጸው መሠረት) ከመደበኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግምገማዎች (HSA) ጋር <u>አንድ ዓይነት</u> ነው።

## Mod-HSAዎች ለምንድን ነው የተዘጋጁት?

ማንም ልጅ ወደኋላ እንዳይቀር (NCLB) የሚባለው ሕግ ስቴቶች የተሻሻሉ ግምገማዎች (Mod-HSA) እንዲያቀርቡ ይፈቅዳል። **እንደዚህ ዓይነት ግምገማዎች ትምህርትና ግምገማ በሚሰጥበት ወቅት** ከትምህርት ደረጃ የይዞታ መስፈርቶች ጋር የተያያዘ የተሻሻለ የትምህርት ውጤት መስፈርቶች ለሚያስፈልጋቸውና ለሚያገኙ ተማሪዎች የተዘጋጁ ናቸው። እነዚህ ተማሪዎች የሚማሩት ሌሎች መደበኛ ተማሪዎች ከሚማሩት ጋር <u>አንድ ዓይነት</u> ትምህርት ሲሆን፣ በስቴቱ ግምገማዎች ላይ ግን ስኬታማ ውጤት እንዲያመጡ የተሻሻለ የትምህርት ውጤት መስፈርቶች ያስፈልጓቸዋል።

## የተሻሽሉ የትምህርት ውጤት መስፈርቶች ምንድን ናቸው?

የተሻሻሉት የትምህርት ውጤት መስፈርቶች የተመሠረቱት የስቴቱ መደበኛ ግምገማ (HSA) በተመሠረተባቸው <u>አንድ ዓይነት</u> የትምህርት ይዞታ መስፈርቶች (የስቴት ፈቃደኛ የትምህርት ሥርዓትና ግምገማ ገደቦች ውስጥ እንደተገለጸው) ነው። ሆኖም Mod-HSAዎች ለየት ባለ መልክ ቀርበው ለየተማሪው የትምህርት ደረጃ የተዘጋጁትን የተለያዩ የፈተና አቅራቦቶችን የያዘውን የክፍል ደረጃ ይዞታ መስፈርቶችን ተማሪዎች ማግኘት እንዲችሉ ያደርጋል። ለምሳሌ ፈተናዎች አጠር መጠን ያሉ ንባቦችን፣ አጠር ያሉ ወይም ከባድ ያልሆኑ ጥያቄዎችን እና ምርጫቸው አነስ ያሉ ጥያቄዎችን የያዙ ይሆናሉ። <u>የ Mod-HSA ይዞታ ከ HSA ይዞታ ጋር አንድ ዓይነት መሆኑን ማወቅ አስፈላጊ ነው።</u> *የፈቃደኛ ስቴት ትምህርት ሥርዓት ማብራሪያን ለማየት እባክዎን www.mdk12.orgን ይጎብኙ።*

## ለምንድነው Mod-HSAዎች በትምህርት ደረጃ ይዞታ መስፈርቶች ላይ የተመሠረተው?

Mod-HSAዎች በየትምህርት ደረጃ ይዞታ ላይ የተመሠረቱት Mod-HSA ውስጥ የሚሳተፉ ተማሪዎች የሚያገኙት ትምህርት በክፍሉ ደረጃ ሆኖ ጥሩ የክፍል ደረጃ ውጤት ማምጣት እንዲያስችላቸው ነው።

## የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች Mod-HSA ውስጥ ለመሳተፍ ምን ዓይነት መስፈርት ማሟላት አለባቸው?

Mod-HSA ውስጥ ለመሳተፍ ብቃት ያለው ተማሪ የግል ግምገማ መረጃውና IEPው/ዋ ላይ ያለው የትምህርትና የአገልግሎት መረጃ ታይቶ ይወሰናል። ተማሪው **ለትምህርትና ግምገማ** ብቁ ነው የሚባለው በሜሪላንድ ዋና ትምህርት ዓላማዎች ውስጥ ያሉትን አልጄብራ/መረጃ መተንተን፣ እንግሊዝኛ፣ ባዮሎጂ፣ እና አስተዳደር ጋር አብረው የሚሄዱትን የትምህርት ደረጃ ይዞታ መስፈርቶችንና የተሻሻሉ የትምህርት ውጤት መስፈርቶችን በመጠቀም ነው።

## አንድ ወላጅ ልጁ Mod-HSA ውስጥ እንዲገባ አልፈልግም ማለት ይችላል?

የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸው ግለሰቦች ትምህርት ሕግ (IDEA) እና NCLB የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች <u>በሙሉ</u> የስቴቱና የአካባቢው ግምገማዎች ውስጥ እንዲሳተፉ ያስገድዳሉ። የIEP ቡድን አባሎች እንደመሆናቸው መጠን፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጃቸው የሚሳተፍባቸውን ግምገማዎች ለመምረጥ ከሌሎች የቡድን አባሎች ጋር አብረው ይሠራሉ። ሜሪላንድ ውስጥ የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸው የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የሚከተሉት ውስጥ ይካፈላሉ፦

- የአልጄብራ/መረጃ መተንተን፣ የእንግሊዝኛ፣ የባዮሎጂ እና የአስተዳደር የሁለተኛ ደረጃ ግምገማዎች (HSAዎች) (ከልዩ ወይም ካለ ልዩ መቀመጫ ዝግጅት፣ እንዳስፈላጊነቱ)
- የአልጄብራ/መረጃ መተንተን፣ የእንግሊዝኛ፣ የባዮሎጂ እና የአስተዳደር የተሻሻለው የሁለተኛ ደረጃ ግምገማዎች (Mod-HSAs) (ከልዩ መቀመጫ ዝግጅት ጋር)

በ IEP ውሳኔ መሠረት ከላይ የተጠቀሱት ግምገማዎች ውስጥ መሳተፍ የማይችሉ ተማሪዎች፥ የሚከተለው ውስጥ ይሳተፋሉ፦

- 10ኛ ክፍል ላሉ ከፍተኛ የመረዳት ጉዳት ያለባቸው ተማሪዎች በማንበብ፣ ሒሳብ እና ሳይንስአማራጭ የሜሪላንድ ትምህርት ቤት ግምገማ (Alt-MSA) ።

## Mod-HSA የትኞቹን ትምህርቶች ነው የሚገመግመው?

Mod-HSA የሚወስዱ ተማሪዎች የሚገመገሙት በአልጄብራ/መረጃ መተንተን፣ በእንግሊዝኛ፣ በባዮሎጂ እና በአስተዳደር ነው። Mod-HSA ውስጥ ላሉ ተማሪዎች፣ ግምገማው የሚመሠረተው በየትምህርት ደረጃ የይዞታ መስፈርቶችና በተሻሻለ የትምህርት ውጤት መስፈርቶች ላይ ነው። እነዚህ መስፈርቶች ተማሪው ከተመዘገበበት ትምህርት ጋር የሚዛመደው ከሜሪላንድ ዋና ትምህርት ዓላማዎች ጋር አብሮ የሚሄዱ መሆን አለባቸው። ስለዚህ የሚሻሻሉት የትምህርት ውጤት መስፈርቶቹ ብቻ ናቸው እንጂ የተሻሻሉት የትምህርት ውጤት መስፈርቶች የተመሠረተባቸው የይዞታ መስፈርቶች <u>አይደሉም</u>። Mod-HSA ውስጥ ያሉ ተማሪዎች የመደበኛ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማን ለማግኘት ማሟላት ያለባቸውን መስፈርቶች ከማሟላት የተወገዱ እንዳልሆነ ማስታወስ አስፈላጊ ነው። <u>አንድ ተማሪ Mod-HSA በአንድ ትምህርት ወስዶ መደበኛ ግምገማ (HSA) ደግሞ በሌላ ትምህርት መውሰድ ይችላል።</u> (ለምሳሌ አንድ ተማሪ Mod-HSAs ዎችን በባዮሎጂ እና እንግሊዝኛ ለመውሰድ ብቁ ሆኖ HSAን ደግሞ በአልጄብራ/መረጃ መተንተን እና በአስተዳደር ለመውሰድ ብቁ ሊሆን ይችላል)።

## ልጅዎን እና አስተማሪውን/ዋን ለግምገማ ለመዘጋጀት ምን አድርገው መርዳት ይችላሉ?

የልጅዎን አስተማሪ በአስፈለገ ቁጥር ስለልጅዎ ትምህርት ሂደት ለማነጋገር ያግኙት። ለግምገማዎቹ ለመዘጋጀት ልጅዎ እና እርስዎ ቤት ውስጥ ልትሠሯቸው የምትችሏቸው እንቅስቃሴዎች አስተማሪዎ እንዲጠቁም ይጠይቁት። ወላጆች/አሳዳጊዎች እና አስተማሪዎች ተባብረው ሲሠሩ ተማሪዎች ይጠቀማሉ።

*የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምሪያ ድህረ ገጽ*

*www.marylandpublicschools.org*

MARYLAND STATE DEPARTMENT OF EDUCATION

Achievement Matters Most